# ግብርና ለብዝሐ ህይወት

## አካባቢያዊ መፍትሄዎችን ወደ አለማቀፉ ፖሊሲ ፈሰስ ማድረግ

የመጨረሻ ሪፖርት




rare

IFOAM ORGANICS INTERNATIONAL

Convention on Biological Diversity

Supported by:

Federal Ministry for the Environment, Nature Conservation and Nuclear Safety

based on a decision of the German Bundestag


የፎቶ ክሬዲት፡ - ጄሰን ሂውስተን ለ ብርቅዬ

## ደራሲያን

ቫሌሪ ግዊነር፣ ኬት ማንል፣ ፍሬድሪክ ስታፕክ

## ማጣቀሻዎች

ግዊነር፣ V. & ማንል፣ K.፣ እና ስታፕክ F.፣ 2021። ግብርና ለብዝሐ ህይወት : አካባቢያዊ መፍትሄዎችን ወደ አለማቀፉ ፖሊሲ ፈሰስ ማድረግ። የመጨረሻ ሪፖርት። በርሊን፣ ጀርመን: ሬር።

በሚከተለው ላይ ኦንላይን ይገኛል: rare.org/report/farming-for-biodiversity/

## ምስጋናዎች

ይህ ሪፖርት፣ እንደፕሮጀክቱ ሰፊው አካል በመሆን፣ ግብርና ለብዝሐ ህይወት በሚለው ሀሳብ ላይ በ2018 በተደረገው የመፍትሄ ፍለጋ ውድድር ላይ አሸናፊ ሆነው ከወጡት ዘጠኝ ድርጅቶች ስራ ላይ ተመስርቶ የሚገነባ ነው። ይህ ፕሮጀክት የአለም አቀፉ የአየር ንብረት ተነሳሽነት (IKI) አካል ነው። የአካባቢ፣ የተፈጥሮ ጥበቃ እና የኒውክሌር ደህንነት የፌደራል ሚኒስቴር (BMU) በጀርመን ቡንደስታግ ተቀባይነት ባገኘው ውሳኔ መሰረት ይህን ተነሳሽነት ይደግፋል። በመፍትሔ ፍለጋው ውድድር አማካይነት መፍትሄዎቻቸውን ላጋሩን በመቶዎች ለሚቆጠሩ ግለሰቦች እና ድርጂቶች፣ የአካባቢ ጥበቃ ላይ ቅስቀሳና ዘመቻ ማድረጊያ አውደ-ጥናቶችን ላስተናገዱት የውድድሩ አሸናፊ ድርጅቶች፣ በአውደ-ጥናቶቹ ለተሳተፉ 227 ግለሰቦች እና በተለይም በዚህ ሪፖርት ላይ በሰነድነት የተቀመጠውን እና በዓለም ዙሪያ ያሉ ማህበረሰቦች ላይ ለውጥን ያነቃቃውን ስራ በመስራት 38ቱን የቅስቀሳ ስራዎቻ በቀጣይነት መስራታቸውን ለቀጠሉት ተሳታፊዎች ምስጋናችንን እናቀርባለን።

ያለ ዶቼ ቬለ እና ፕሮጀችቱ ግልቶ የሚታይበትን ሁኔታ በመፍጠር፣ አብረውን የሰሩት 27 + ሚዲያዎች፣ መፍትሄዎችን ለህዝብ በማስተናገድ ረገድ ያለ ፓኖራማ እገዛ እና ያለ ወጣት የግብርና ልማት ባለሙያዎች (YPARD)፣ የአለም አቀፉ የመሬት ገጽታ መድረክ (GLF) )፣ እና የተባበሩት መንግስታት የምግብ እና እርሻ ድርጅት (FAO) በአውታረ መረቦቻቸው ውስጥ የሚያደርጉት ድጋፍ እና አበረታች ማስተዋወቅ ባይጨመርበት ኖሮ የፕሮጀክቱ ቅንጅታዊ ኃይል እንዲህ ጎብቶ መውጣት ባልቻለም።

ከዘጠኝ ወርክሾፖች እና 38 የዘመቻ ሪፖርቶች የነበረውን ውሂብ በማደራጀት እና በማጠናቀር ስለሰራች ፋጢማ ራሚስን ማመስገን እንፈልጋለን። ይህ ሪፖርት ከፖል በትለር፣ ዱልስ ኢስፔሎሲን፣ ጋቦር ፊጌዝኪ፣ ኮንራድ ሆትፍሌሽ፣ ዶ/ር አዳም ለቪን፣ ሺያንግ ሊ፣ ሊዛ ሺንድለር-ሙሬይ፣ ፍሬድሪክ ስታፕክ እና አሪየን ስቴንስ-ሚር ከተሰጡት አስተያየቶች ተጠቅሟል።

## ማርትዕ እና ዲዛይን

ኪላ ቲምበርላክ

# የስራ አስፈጻሚ ማጠቃለያ

በግብርና ለብዝሐ ህይወት  የመፍትሄ ፍለጋ ውድድር የብዝሐ ህይወት ጥበቃ እና የግብርና ምርትን ለማስማማት ማህበራዊ መፍትሄዎችን ለመጠየቅ ቀጥተኛ ሙከራ ነው። ከህዝብ-የመነጨ ቅርጸትን በመጠቀም፣ ውድድሩ ከ 86 ሀገራት 338 ማመልከቻዎችን ስቧል። ብዙም ካልተሞከረው አንስቶ  ከፍተኛ ጥናት እስከተደረገበት ድረስ፣ መፍትሄያቸው የግብርና ማህበረሰቡን እና ቤቴ ብለው የሚጠሩትን አካባቢዎች ለመጥቀም ተስፋ ያላቸው ልማዶችን መተግበር ላይ ያተኩራል። አቀራረቦቹ እና ስኬቶቹ ግብርና  እና ብዝሐ ህይወት የሚጋሩት ነገር የላቸውም የሚለውን በሰፊው የተያዘውን አስተሳሰብ ያስምርበታል፣ ነገር ግን፣ ራሱን የሚያጠናክር መሆን ያለበት መሆንም የሚችህል ነው። በተጨማሪም፣ በአለም ዙሪያ ያሉ ትንንሽ ፕሮጀክቶች አለም አቀፋዊ ግቦችን የለወጡበትን ተጨባጭ መንገዶች እና ወደ ዘላቂ ልማት በማምራት ወደ እውናዊ ልማድ ለማምጣት መመሪያን ያሳያሉ።

በ 2017 ከነበረው ውድድር ጀምሮ፣ የዓለምን ብዝሐ-ህይወት ጥብቆና ተንከባክቦ የማቆየቱ አስፈላጊነት ግንዛቤ አድጓል፣ ምግባችንን እንዴት እንደምናመርት እና እንዴትስ እንደምንጠቀመው የሚያሳዩ መንገዶችን ጨምሮ፣ ከስነ ምህዳር አያያዝ ጋር ተስማሚ አቀራረቦች እየጨመሩ ነው። የተፈጥሯዊ ሀብቶችን መጠበቅ ለእያንዳንዱ መዋእለ ንዋይ ለተደረገው አንድ ዶላር ዘጠኝ ዶላር የኢኮኖሚ ጥቅማ ጥቅሞችን በማምጣት የገንዘብ ምንጭ እንደሆኑ የሚደግፈውን መከራከሪያ ለመደገፍ ተጨማሪ ማስረጃዎች እየመጡ ነው።

ቢሆንም፣ እነዚህን ሊመጡ የሚችሉ ጥቅማ ጥቅሞችን ለማግኘት፣ ውድ ስነ ምህዳሮችን እና የእነርሱን ብዝሐ ህይወት ለመጠበቅ የሚሰጡት ድጎማዎች እና ድጋፎች እስከታችኛው የማህበረሰብ ደረጃ  ድረስ ወርደው መድረስ አለባቸው። የመጠነ-ትናንሽ አርሶ አደር ማህበረሰቦች ድርጊቶች እንደ መጠነ-ትላልቆቹ ስትራቴጂዎች ሁሉ ለዓለም አቀፋዊው ማህበረሰባችን ወሳኝ መሆናቸውን ለመገንዘብ በሚያስችል መልኩ የተቀየሱ መሆን አለባቸው፣ እንዲሁም በአካባቢ ደረጃ የሚገኙ ደጋፊዎች ለማስፋፋት እና መፍትሄዎቻቸውንም ወደሚለካ ደረጃ ከፍ ለማሳደግ የሚያስችህላቸው ግብዓቶችን ማቅረብ የሚችል መሆን አለበት።

በግብርና ለብዝሐ ህይወት  የመፍትሄ ፍለጋ ውድድር የማህበራዊ ደረጃ መፍትሄ ውስጥ ያሉ ትንንሽ መዋእለ ንዋዮች ከግምት ውስጥ ወደሚገቡ ትርፎች ሊመሩ እንደሚችሉ አሳይቷል፤ ለተሳታፊዎች እና ለፕሮግራሞቻቸው ብቻ ሳይሆን በጣም በስፋት ሊሆን ይችላል። ዘመቻ ለጥበቃ (C4C) ወርክሾፖችን ከ 12 ሀገራት ከተወከሉ 38 የተለያዩ ድርጅቶች ከመጡ ተሳታፊዎች እንዲያዘጋጁ ከውድድሩ ዘጠኝ መሪ ፕሮጀክቶች ተመርጠዋል። ወርክሾፖቹ፣ በ IFOAM ኦርጋኒክስ ኢንተርናሽናል እየተመራ፣ የሬር የ C4C ስልትን፣ ዘላቂ ያልሆኑ ልማዶችን መቀየር አላማው ያደረገ የማህበራዊ ገበያ ዘመቻ እንዴት እንደሚዘጋጅ እና እንደሚተገበር የሚያስተምረው፣ ከኦርጋኒክ ግብርና ቴክኒኮች እና ገበያ ስልጠና ጋር አጣምሯል።

የ C4C ተሞክሮ እና ዘመቻዎች 227 ሰልጣኞች፣ 43,000 ኢላማ የሆኑ አድማጭ/ተመልካች አባላት፣ እናም ከ 570,000 የሰፊው ማህበረሰብ አባላትን ደርሷል። እነዚህም የለውጥ እንቅስቃሴ መሪዎች አዲስ ካድሬን ለመፍጠር በተሳታፊዎች መካከል፣ ከአዲስ የክህሎት ስብስቦች ጋር፣ በጣም ትልቅ የግል ውጤታማነትን አምጥተዋል። የእነርሱ ሞገዳዊ ውጤቶች ለተሻለ የመሬት ቁጥጥር እና ጤናማ ስነ ምህዳር ብቻ አይደለም የመሩት። ትልልቅ የማህበረሰብ ተሳትፎ፣ የሴቶች እና ወጣቶችን  የሚጨምር አካታችነት፣ ጠንካራ ማህበራዊ ጥምረት፣ የተሻሻለ የኑሮ ሁኔታ እና የኑሮ አማራጮች፣ እና የነባር ሰዎች እና ሀብቶች የታደሰ ዋጋ የመሳሰሉ ውጤቶችን ፈጥረዋል።

የ C4C ስልጠና ውጤታማነት  ዋና ምክንያቱ የሚገኘው የስነ-ባህሪ ሳይንስ ላይ የተመሰረተ  እና ለብዝሐ ህይወት ስጋቶች እና እነዚህን መየቅረፍ መፍትሄዎች ላይ ደግሞ የሰው ባህሪያት ዋና መሆኑ ላይ ነው። የወርክሾፖቹ መሳሪያዎች እና ምርቶች በማህበራዊ ግንኙነቶች እና የሰው ልጅ ባህርያትን በሚጎዱ ተፅእኖዎች ውስጥ ይሰራሉ፤ እንዲሁም ለውጥን ለማነቃቃት፣ ቀላል ለማድረግ እና እንደ አዲስ  አማራጭ ለማስረጽ መንገዶችን ያቀርባሉ።

በሚዛን ላይ ወጥቶ ሲለካ፣ የእርሻ ምርትን እና የብዝሐ ህይወት ጥበቃን ለማስታረቅ፣ የባህሪ ለውጦች እና ማህበረሰቡን መሰረት ያደረጉ መፍትሄዎች ጥልቅ ለውጥ ሊያመጡ ይችላሉ። የገጠር ኢኮኖሚን ሊያጠናክሩ የሚችሉ የምግብ እና የመሬት አጠቃቀም ስርአቶችን ለውጥ ሊያበረታቱ ይችላሉ፤ ይህም በጣም አካታች እና የምግብ ደህንነት የሚሰጡ ያደርጋቸዋል፤ ይህም መጠነ ሰፊውን የዘላቂ ልማት ግቦች፣ የድህረ-2020 የ UN አለም አቀፋዊ የብዝሐ ህይወት አውታር እና የአየር ንብረት ስምምነት ኢላማዎች፣ ለማሳካት አለምን ያስጠጋል።

የዚህ ሪፖርት ገጾች ትንንሽ ማህበረሰብን መሰረት ያደረጉ እና የሚመሩ ዘመቻዎች የሰው ልጅ ግንኙነቶች እና የባህሪያዊ ለውጥ ሳይንስ ትምህርቶች ለራሳቸው ጥቅም እና ለእኛ ጥቅም የእርሻ እና የብዝሐ ህይወት ትምህርቶችን ለማስማማት እንዴት እየጠቀሙ እንደሆነ ይገልጻል። ከታች የሚነሱ መፍትሄዎች ህይልን፣ እና በአካባቢያዊ እርምጃ እና በአለማቀፍ አላማዎች መካከል ያሉትን አስፈላጊ ቅንጅቶች ያሳያሉ። የተለያዩ ባለድርሻ አካላት—ከከፍተኛ ደረጃ ለጋሾች እና ፖሊሲ አውጪዎች እስከ ንግዶች፣ መዋእለ ንዋይ አፍሳሾች፣ አጥኚዎች፣ ተጠቃሚዎች እና ራሳቸው ማህበረሰቦች—እንዴት መጠነ ትንሽ መፍትሄዎችን፣ እና መጠነ ሰፊ አቅማቸውን እንደሚደግፉ ተስፋ እና የሚዳሰስ ምክረ ሀሳብ ይሰጣሉ።



Convention on Biological Diversity

Supported by:

Federal Ministry for the Environment, Nature Conservation and Nuclear Safety

based on a decision of the German Bundestag

የፎቶ ክሬዲት፡ - ጀሰን ሂውስተን ለ ብርቅዬ